# ሠወድስ ኦነግ

## «የኦሮሞ ህዝብ ከዴሞክራሲ የሚፈራው ነገር የለም» - ሌንጮ ባቲ

ከያሬድ ጥበቡ

ባለፉት አምስት አመታት በአዝጋሚ ሂደት ሲጓዝ የቆየው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር የአመለከከት ለውጥ፡ እነሆ እመርታ ወሰደ ። በዚህም ብልህ ዕርምጃው «እኛ በገላጋይነት ከሌለን፡ ኦሮሞና አማራ አንገት ላንገት ይተራረዳል» ብሎ ሲያስፈራራን የከረመውን የወያኔ መንጋ አሳፈረው ። «የኦሮሞ ህዝብ ከዴሞክራሲ የሚፈራው ነገር የለም» የሚለው የሌንጮ ባቲ የሃቅ ድምፅ ሲያስገመግም፡ ወያኔ አለቀሰ፡ ኢትዮጵያ ደግሞ ዕልልታዋን አቀለጠችው ። ኢትዮጵያችን፡ ቤቱ መግቢያ አጥቶ ይሁን ጠፍቶት በረሃ ለበረሃ ሲነከራተት የነበረው ልጇ ወደ ዕቅፏ ሲመለስ፡ ቁጠማ ጎዝጉዛ፡ ዕጣን አያይዛ ብትቀበለው ሲያንሳት ነው ።

አርባ አመት በምድረ በዳ ተንከራተው በረሃብና ቸነፈር፡ በሐሩርና ቁር ተጠብሰው፡ የአስርቱ ቃላት ዕውነት እንደተገለፀላቸው የሙሴ ዘመን ዕስራኤላውያን፡ የኦሮሞ ነፃነት ግንባርም በሠላሣ አመት ዕንግልቱ፡ በደርጉም በወያኔም እሳት ተጠብሶ፡ ምላሱ እንኳዋ ሳይቀር ተቆርጦ፡ ከአበሳውና ወፌ ኢላላ ግርፋቱ መራራ ትምህርት ቀምሮ የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ የበኩር ልጅነቱንና «አንጋፋነቱን» አምኖና ተቀብሎ ወደ ኢትዮጵያ ዕቅፍ ሲገባ፡ «የኛማ ሙሽራ»ን እየዘመርን ብንቀበለው አይበዛብንም ። ምክንያቱም እንደ ወያኔ በተራ ብልጣብልጥነት ለሌሎች ፍጆታ ብሎ ሳይሆን፡ ከሕሊናው አፍልቆ፡ አምጦ የወለደው ዕምነቱ በመሆኑ ደስ ልንሰኝ ይገባል ።

ይህን «በኢትዮጵያ ዕቅፍ ውስጥ የመኖር ተስፋ ያዋጣል ወይ?» ብሎ ከራሱ ጋር መክሮበታል ። አልቅሶበታል ። ቆዝሞበታል ። ከአመታት ጭንቅ በኋላ ሲገላገልም፡ ብላተናው ዕፁብ ድንቅ እንጂ ነው ። ቤተሰቡን በትና፡ ዘመድ አዝማዱን አስለቅሶ፡ የተወለደ ፅንስም አይደለም። ሁሉንም እንዳሰባሰበ፡ ቤተ ዘመዱ ቀርቶ የሩቅ የወንዙ ልጅ ሁሉ በፍቅር እየተጠባበቀው የተወለደ ህፃን ነው ። እንደ ብላተናነቱም ቢኮላተፍ፡ እደግ ተመንደግ እንጂ፡ «እንዴት ተኮላተፍክ?» እደማንለው ዕሙን ነው ። ታዳጊን ልጅ ይመርቁታል እንጂ አይረግሙትም ። ይልቁንስ «የሚያድግ ልጅ አይጥላህ» ነው እመውም የሚሉት ።

በወያኔ አገዛዝ የዘር ዕልቂት በታወጀባት ኢትዮጵያ፡ የወያኔን ተራ ብልጠት እምቢኝ ብሎ፡ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር፡ «እኛ ጨዋታ አንፈልግም፡ መፍትሄ እንጂ! » ሲል፡ በፊንፊኔ አማልሎ ኪሱ ከስገባ በኋላ፡ ለዳግመ ዕርድ ያሰበውን ወያኔ፡ ዐይንህ ላፈር ማለቱ ታላቅ ዜና እንጂ ነው ። በዚህ አግራሞት ተውጬም፡ «ዕውን ይሄ የኢትዮጵያ አምላክ የሚሉት  ኃይል ይኖር ይሆን?» እያልኩ ራሴን መጠየቄም አልቀረም ። «ወያኔ ስለተዳከመ ነው ለውይይት የጋበዘን፡ ፊንፊኔን እንከችሁ ያለን» ብሎ ኦነግ ግምኛ ሊያስብ ይችል ነበር ።  ግን «የለም፡ ሁሉን የፖለቲከ ሓይሎች ያከተተ ኮንፈረንስ ጥራና፡ በዚህ በ11ኛው ሰአት ዕድሜህ ፡ ሳይጨልምብህ ራስህን አድን» ብሎ፡ ኦነግ መሪነቱን ሲይዝ፡ ይህን እንደ ተአምር ብናይና፡ የኢትዮጵያን አምላክ ባህርይ ብናጠይቅ ተገቢ እንጂ ነው ።

በእኔ ግምት የምንሊክ ዕምዬ ባህሪ የመነጨው፡ ከአደገበት የአንኮበር ቁር ሳይሆን፡ ከአማከሪዎቹ የኦሮሞ ፊታውራሪዎቹና ደጅ አዝማቾቹ ሆድ ሰፊነት ጭምር ይመስለኛል ። የዘመናዊት ኢትዮጵያን ከስማ የተከለ፡ የድንኩዋኗን ዋልታ የያዙ፡ መወጠሪያውን ከችከል ያሰሩ የምንሊክ ባልደራሰችና አዝማቾች ኦሮሞዎች እንጂ ነበሩ ። ሆደ ሰፊነትንም፡ ይዘውት ከመጡት ማር፡ ቅቤ ፡ ወርቅና፡ የሰው ጉልበት ብቻ ሳይሆን፡ ከገዳ ሥርአታቸው ከጨለፉት የመቻቻልና የፍቅር ባህላቸውም፡ የምንሊክን አዳራሽና ልቦና ሊያጥኑት በመቻላቸው ነው ከነገስታቱ ሁሉ ተለይቶ ምንሊክን ዕምዬ ያሰኘው ብዬ

አስባለሁ ። ስለሆነም፡ የኦነግ ፊቱን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ፡ ተራ የሓይል ሚዛን ጉዳይ፡ ወይንም የወያኔን ዘረኛ ጦር የመመከቻ ጋሻ ብቻ ሳይሆን፡ በይቅር ባይነትና መቻቻል፡ በሆደ ሰፊነትና በሐሳብ ጦርነት ለምንመሠርታት መፃኢቱ ኢትዮጵያ የክብር ደንጊያ ጭምር ነው ። ከዛሬና ከነገ ዘልቀን፡ የተነገወዲያውን በህሊናችን አማትረን ዐይተን፡ ንሴብሆ እያልን በሽብሽባ ልንቀበለው ተገቢ ነው ። ፈረንጆቹ፡ የዛሬው ፍፁም ፀጥታ ከማዕበሉ መነሳት በፊት ያለውን ሠላም ይመስላል እንደሚሉት፡ እኛም በተቃራኒው፡ የዛሬው ፍጅትና ዋይታ የነገውን ጥልቅ ሠላም የሚያዋልድ የምጥ ጩኸት አድርገን እንውሰደው ።

በኦነግ መገለልና የዳር ታዛቢነት የተከፋነው፡ ለምን የተለየ ሓሳብ ኖረው ብለን አይደለም ። ለብዙዎቻችን ጉራጌነታችን ወይም አማራነታችን የትጋ አቁሞ፡ ኦሮሞነታችን የትጋ እንደሚጀምር ለመለየት እንኩዋ የማንችልበት ውስብስብ ውስጥ ነው የኖርነው። ባለቅኔው ሰለሞን ዴሬሳ እንደጠየቀን «በአያቶቻችን በር ስንት ሠራዊት ማለፉን እናውቃለን?» ነው ነገሩ ። ለብዙዎቻችን ኦሮሞነትንና ኢትዮጵያን መነጠል አይቻለንም ። የኢትዮጵያን አርማ በአለም አቀፍ መድረክ የሚያውለበልቡልን የኦሊምፒክስ ጀግኖቻችን ባመዛኙ ኦሮሞዎቸ ናቸው ። ታላቁ ባለቅኔያችን ፀጋዬ እንዲሁ ። ኣባት የጦር መሪያችን ጃጋማ ኬሎ ያለጥርጥር ። ጥላሁን ገሠሠን እኔ ምን አውቅቼ። ኦነግ ሲያኮርፍ የምናጣው ቡናና ወርቁን ሳይሆን፡ እነዚህን ጌጦቻችንንና መኩሪያ መጎናፀፊያዎቻችንን ጭምር ሰለሆነ ነው፡ የኦነግ ኩረፊያ ያስጨነቀንን ያህል፡ የመመለሱ መለከት ደግሞ ገና ከሩቅ ሲሰማ ሰውነታችን በደስታ የሚወረረው። የኦሮሞው መለከት ድምፅ እየቀረበ ሲመጣ፡ በአማራ ዋሽንት፡ በትግሬ ከበሮ፡ በጉራጌ ዳንኪራ፡ በደቡብ ዕምቢልታ ታጅቦ የሚወጣው ህብረ-ድምፅ፡ ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አእምሮ ሳይሆን፡ ከውስጠ-ህሊናው የሚንቆረቆር ታላቅ ሲምፎኒ እንደሚሆን ጥርጥር የለኝም ። የነገ ሰው ይበለን ።

በመጨረሻም፡ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር መልዕክተኛ እንዳለው፡ ወያኔ የጭለማውን መቃረብ ዐይቶ በአስራ አንደኛው ሰአቱ ላይ ከጥፋቱ ለመመለስና ሁሉንም የፖለቲክ ሃይሎች ያሳተፈ (እንደኔ እምነት የራሳቸውን ጥቅም ከሚያሰላስሉና ከሚሸርቡ የነጭ «ታዛቢዎች» የፀዳ) ጉባኤ ለመጥራት ፈቃደኛነቱን ከላስታወቀና፡ ለዚህም ፈቃደኛነቱ ምልክታ እንዲሆን የፖለቲከ እስረኞችን ከልፈታ፡ ዕድሜውን ለማሳጠር ዙሪያ መለስ ትግሉ መፋፋም ይኖርበታል ። ታላላቆቹን የኦሮሞ፡ አማራና ጉራጌ ፀረ-ፋሺስት አርበኞች የወለደው የአመያ፡ የሆሮ ጉድሩ፡ የመንዝና ተጉለት፡ የኢተያ፡ የመርሃ ቤተ፡ የጊቤ ፡ የከሰም በረሃ ፡ የወሊሶ፡ የሰላሌ ከባቢዎችን፡ የአዲስ አበባን ዙሪያ መቀነት በትጥቅ አመፅ አነሳስቶ፡ ወያኔን መውጫ ማሳጣት ግዴታ እየሆነ እየመጣ ነው ።

ገረሱ ዱኪን፡ አበበ አረጋይን፡ ጃጋማ ኬሎን፡ ከበደ ብዙነሽን፡ ሀይለ ማርያም ማሞን የመሰሉ ጀግኖች የፈጠረች ሃገር፡ የወላድ መከን አለመሆኗን ለወያኔ ማረጋገጥ የምትገደድበት ቀን እየተቃረበ ነው ። የኦነግ የምስራች የዚህ መፃኢ የትግል ርብርብ አንድ አከል ነው ። ተስፋ የሚፈነጠቅ ዘመን ከፊታችን ይጠብቀናል ። ያለቀሱ እናቶች እንባ ይደርቃል ።

ሞት ለዘረኞች !!